March 20, 2009

"በአላህ ስም እጅግ በጣም ርኅሩኅ አዛኝ መሃሪ በሆነው።"

እኛ ኢትዮጵያውያን አብሮ ባኖረን አብሮ በሚያኖረን ቃል-ኪዳን ተሳስረናል። ይህንን እፁብ ድንቅ የሆነ ቃል-ኪዳን ጠብቀን ለቀጣዩ ትውልድ እንደምናስተላልፍ ስንገልጽ ታላቅ ደስታ ይሰማናል። ስለምን ቢባል የምንከተለው ሐይማኖት - ኢስላም- ተቻችሎ የመኖር ቃል-ኪዳንን በፅኑ ያስተምረናልና -- ነው።

ድህነት፣ የተፈጥሮ ችግር፣ ረሃብና በሽታ በሚፈራረቁባት ውዷ እናት አገራችን ላይ እንደማንኛውም ዜጋ የሚደርሰውን ችግር ብንጋፈጥም፣ እንደማንኛውም ዜጋ ችግሩን ብንጋራም ሙስሊም ሆኖ በምድረ-ኢትዮጵያ መኖር ተጨማሪ ችግር እንዳለው፤ ተጨማሪ ችግር እንደነበርው ከታሪካችን ማህደር ልንፍቀው ከዘመኑ የኑሮ ተሞክሮ ልናገለው የማንችለው አሳፋሪ የታሪካችንና የህይወታችን ገፅታ ቢሆንም በኢትዮጵያዊነታችን እንደማንኮራ ስንገልጽ ልባዊ ደስታ ይሰማናል።

ኢትዮያዊ ሙስሊም ሆኖ መኖር ፈታኝ ቢሆንም ይንን ፈተና የሚያቀናጁት ጥቂት ጨቋኝ ኃይላትና አክራሪ የሐይማኖት መሪዎች ናቸው። ዛሬ ደግሞ ዓለም በጨቋኞችና በአክራሪዎች የተንገፈገፈች በመሆኗ፤ እኛም ዛሬ እዚህ ቀመን ለጨቋኞችና ለአክራሪዎች «በቃችሁ አትበጥብጡን- አታበጣብጡን» በማለት ፅናት የተሞላበትን ወደፊት እንጂ ወደኃላ የማንመለስበትን ሰላማዊ ድምፃችንን በወኔ እናሰማለን።

ተንኮል በፍቀር ይሸፈናል። ለዘመናት እንድንተላለቅ ሲዶለትብን፤ ፍቅርን ተጋርቶ ፍቅርን ላጋራን፣ ከሰላም ተዋውሎ ሰላምን ላዋዋለን፣ በባህል በዘር በጋብቻ በልቅሶ በሰርግ በወሊድ ወቅት እንደተቀራኘው ሁሉ ለተቀራኘን፤ ውድ ለሆነው ኢትዮጵያዊው ህዝበ-ክርስቲያን ያለንን አክብሮት እየገለጽን ነገም በዚሁ ሰላማዊ የአኗኗር ዘይቤ ከክርስቲያን ወገኖቻችን አብረን እንደምንኖር በደስታ እንገልፃነን።

እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ1966 ባደረግነው ታላቅ ህዝባዊ ሰላማዊ ሰልፍ ላይ በአዲስ አበባ ጎዳኖች ድምፃችንን ከፍ አድርገን ያስተጋባንነው በልቦናችንንና በአንደበታችን የዘመርነው የቃል-ኪዳን ተምሳሊት የማንነት ምልክት የሆነ መፈክር ነበር ዛሬም ከ35 ዓመት በኋላ እንደግመዋለን።

> "ኢትዮጵያ አገራችን!
> ክርስቲያን ወንድማችን!
> ይመስክር ደማችን!
> አንድ ነው እጣችን!!"

አንድ ህዝብ በመሆናችን አንድ እጣ ነው ያለን! አንድ ህዝብ በመሆናችን አንድ ተስፋ ነው ያለን። የኢትዮጵያ ህዝብ በዘር በብሔር በሐይማኖት ቢለያዩም እንደ አንድ ገላ ነው። የሙስሊሙ መጎዳት፣ የሙስሊሙ መጎሳቀል፣ የሙስሊሙ ሰብዓዊ መብት መገፈፍ የክርስቲያን ወገኑም ሆነ የሌላው የጋራ ችግር ነው። ፍቅርን ባስተማሩን ኢየሱስ (አ.ሰ.)፣ ርኅራኄን ባስተማሩን ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) የጽድቅ መንገድ በህብረት ተሰማርተን ይህንን መጤ የጭቆና አመራርና በሐይማኖት ስም

First Hijra Foundation

ስውር የፖለቲካ ዓላማ ያለውን ፅንፈኝነትን በጣምራ ሳይከፋፍሉን፣ ሳያጫርሱን፤ በፍቅር በአንድነትና በሰላም አጥምደን ይዘናቸው የሰብዓዊነትን ሁለንተናዊ ስንደቅ ከፍ አድርገን እናውለበልብ።

ይህ ሰላማዊ ሰልፍ የሰላም ጥሪ ነው። ይህንን የሰላም ጥሪያችንን የሰሙ ኢትዮጵያውያን ሁሉ የጋር ለሆነችዋ አገር ህልውና ቅድሚያ በመስጠት በሰላም - ለሰላም እጅ - ለጅ ተያይዘው በአንድነትና በልማት ወደኋላ ያስቀሩንን ጭቀናና በሐይማኖት ሽፋን የሚከናወነውን ዘልማዳዊ የአሰራር ዘይቤ የጥፋት እንጂ የልማት ተምሳሊት ባለመሆናቸው በቃችሁ፤ ኢትዮጵያ ልማት እንጂ ጥፋትን አትሻም እንበላቸው።

የዛሬን የሰላም ድምፃችንን ለማዳፈን ከዓይናችን እይታ ዘወር ብለው ተበታትነውም ይሁን ተሰባስበው በመዶለትና በማስዶለት፤ በማደምና በማሳደም በሐይማኖት ስም ስውር የፖለቲካ ዓላማን የሚያራምዱ ወገኖች ይህንኑ የሰላም ጥሪያችንን ሰላማዊ ዓላማን በማጣመም የራሳቸውን ጥፋት በኛ በሰላም ፈላጊዎቹ ላይ በማላከክ በሐይማኖት ስም የፖለቲካ ቅዠት በመቃዠት ስለማይቆጠቡ አብሮ ባኖረን አብሮ በሚያኖረን ሰላም ፍቀር ተቻችለን እንኖራለን እንጂ በቅዠት አንመራም እንበላቸው።

እነዚህ በእምነት ስም የፖለቲካ ዓላማ ያላቸው ፅጉር ልውጦች በየእምነት ማዕከሉ፣ በየማህበራቱ፣ በየሰው ቤት ካሊያም በየአደባባዩ ዓላማቸውን ለማሳካት እንደ ጥላ ስለሚከለሉን እምነትን የግል አገርን የጋራ አድርገን

ለመከፋፈል ቦታ የለም!<br>
ለፅብ አጫሪነት ቦታ የለም!<br>
ለጭቆና ቦታ የለም! --- እንበላቸው!!

አብሮ ያኖረን አብሮ የሚያኖረን ቃል-ኪዳን አይታጠፍም። ኢትዮጵያውያን በአንድነት እንኖራለን! ኢትዮጵያውያን ተቻችለን እንኖራለን! ኢትዮጵያውያን በሰላም እንኖራለን! ይሔ ቃላችን ነው፤ ይሔ ተስፋችን--- አላህ ይርዳን። አሚን!!

አመሰግናለሁ።

(ከፈርስት ሂጅራ የሰላማዊ ሰልፍ አስተባባሪ ኮሚቴ)

First Hijra Foundation

March 20, 2009

“በአላህ ስም እጅግ በጣም ርኅሩኅ አዛኝ መሃሪ በሆነው።”

ኃያል ልዑል የሆነው አላህ (ሱ.ወ.) ይመስገነንና የምንከተለውን ሐይማኖት ባለቤት ያደረገችን የምንወዳትና የምንናፍቃት አገር አለችን። ከአገርም ልዩ አገር! የጥንት ስልጣኔ ምስጢር የአብረሃማዊ ሐይማኖት ቀመር! ---- ኢትዮጵያ!

እናት አገራችን ኢትዮጵያ የማንነታችን መሰረት ዞሮ መግቢያ የምንላት፣ የተለያዩ ዘርና ብሔርና ያካተተች፣ የተለያዩ ባህልና እምነቶችን በካዝናዋ ያስቀመጠች፣ የጋር እናት የጋራ አገር--ኢትዮጵያ!

ይህቺን ሰው ዘራሽም ብቻ ሳይሆን ወፍ ዘራሽም በሚበቅልባት ለሟ አገር፣ ወንዞቿ ሞልተው ለም አፈሯን ሸርሽረው የጎረቤት አገርን የምትመግበዋ አገራችን፣ የስልጣኔ ምንጭ እንዳልሆነችው ሁላ ስልጣኔ ተነጥሏት ረሃብና በሽታ ድንቁርና ተባብረው እያንገሏቷት-- እንዲህ ተጎሳቁላ ስትታይ “ለምን ይሁን?” ብሎ ከስር ከመሰረቱ ማየቱና መመርመሩ ኢትዮጵያዊ ግዴታ ነው።

እኛም ሰላምን ያልን የሰላም ወገኖች ዛሬ ለሰላም ተሰባስበን ኢትዮጵያን እግር-ተውርች አስሮ አታድጊም፤ አትበለጽጊም ያላትን ችግር ለሰማው ወገን ዳግም ለማሰማት፣ ላወቀው ወገን ዳግም ለማሳወቅ፣ ለዘነጋው ወገን ለማስታወስ፣ ለካደው ወገን ለማሳመን እዚህ የቆምነው። የኢትዮጵያ ችግር ከስር ከመሰረቱ ይመርመር። መቻል እያመዘነ መቻቻል አለ ተብሎ ተድበስብሶ አይነገር፣ ቂም ይዞ ፀሎት፣ ሳል ይዞ ስርቆት እንደሚባለው--- ይህንን እውነት በሰላማዊ መንገድ ለመናገር ነው እዚህ የቆምነው።

“ማን ይናገር የነበረ፣ ማን ያርዳ የቀበረ” ተብሎአልና ኢትዮጵያዊ ሆኖ መኖርን አይተነዋል-እናውቀዋለንም! በተለይም ሙስሊም ኢትዮፕያዊ ሆኖ መኖር!.... ከዘመን ወደዘርመን ከትውልድ ወደ ትውልድ የበደል ናዳ ሲወርድብን ከዛሬ ነገ ከአምና ዘንድሮ ይሻላል ብለን፣ ፍቀርን መርጠን ስለላምን መርጠን እስኪያልፍ ያለፋል ብንልም የለም “ እስኪያልፍ ያልፋል” ማለቱም በዛባችሁ ለማለት ይመስል የሚሰጠን የቤት ሥራ ይብቃ ለማለት ነው ዛሬ የተሰበሰብነው።

በመንግሥት አሰራር ስጥ ሰርገው የገቡ የየስርዓት-ማህበሩ ጥቅማ-ጥቅም ተጠቃሚዎች በቅዱስ ስም ማህበር የመሰርረቱ የጥፋት ሀይሎች፣ በፅድቅ ስም ጥላቻን የሚያስተምሩ ሰባኪ ተብየዎች በሰው ቁስል እንጨት ሰደድ እንደሚባለው “ችሎ መኖር “ ለሙስሊሞች በዛባቸው ይባል ዘንድ “ኢትዮጵያ የክርስቲያን ደሴት ናት! አንድ አገር አንድ ሐይማኖት! ዜግነት በመጠመቅ” ቀረርቶዎችን ሁካታና ብጥብጥን ለፍጠር ያሰሙን ገቡ። የሰማነውን ሰማን ያየነውን አየን ግና ይህንን የመሰለውን ኋላ ቀር ድንፋታ በዓለማችን ላይ ቦታ እንደሌለው በቁርጠኝነትና በሰላማዊ ድምፅ ዛሬ ልናሰማቸው ነው የተሰበሰብነው።

ዛሬ እዚህ የተሰበሰብነው ለሙብት ነው! ዛሬ እዚህ የተገኘነው ህግ-መንግስት ይተግበር ለማለት ነው። ሙብት ስንል ዶሮን ሲያትልሏት በመጫኛ ጣሏት የሚባለውን ሙብት አይደለም። ሙብት! አዎ ሙሉ ህግ-መንግሥታዊ ሙብት! ሙሉ ሰብዓዊ ሙብት! ሙሉ ስብዓዊ ሙብት ያልተሸራረፈ ሙብት!

First Hijra Foundation

እንደሌላው ዜጋ ሁሉ የህገ-መንግሥት ባለቤት መሆናቸውን እየታወቀ ለሌላው በአካፋ ለኛ በማንኪያ የሚሰጠን መብት ላለመደራደርም ላለመቀበልም ነው እዚህ የተሰበሰብነው።

ልብ ያለው ልብ ይበል!

መብት እኩልነት በነፃ የሚገኙ ሰብዓዊ የመፈጠር ገፀ-በረከቶች ቢሆኑም የግዜና የትግል ዋጋ በላያቸው ላይ ጨምሮ መብትና እኩልነት ከባለቤቱ ተነጥቀው ሲወደዱ እርግጡን እያለን ለመከራከር ሳይሆን በመብትና በእኩልነት ላይ ተብሎ የሚደረገውን የዋጋ መናር እንቃወማለን ለማለት ነው እዚህ የተሰበሰብነው።

ልብ ያለው ልብ ይበል!

ሐይማኖት በዜግነትና በአገር ፍቅር ስሜት ላይ ሲጠቀለል አደገኛና አክሳሪ መሆኑን ከሌሎች አገሮች የታሪክ ሒደት ተምረናል። ይህ አደገኛ የሆነው የሐይማኖትና የዜግነት ትስስር በተከበረው የክርስትና እምነት ተጠምጥሞ ኢትዮጵያን ለከፋ ችግር አጋልጦ ህልውናዋን አደጋ ላይ ሊጥል በመሆኑ ይህ ስራዓተ አልባኝነት በኛ የህይወት ዘመን አይፈፀምም አይሳካምም የሚለውን ሰላማዊ ጥሪ እናሰማለን።

የተከበራችሁ ውድ ኢትዮጵያውያን ሆይ! አሁን ያለውን ህገ-መንግሥት ለማምጣት የህይወት መስዋዕትነት የከፈሉት ሙስሊም የአክሱም ልጆች አጥንት ተበታትኖ የመቀበር ዕድልን ያገኙትም መቃብራቸው በግልፅ እየታየ በህይወት ትተዋቸው የሄዱትን ቤተሰቦቻቸውን መስጂድ አትሰሩም ብሎ ህገ-መንግሥታዊ መብትን በግልፅ መንፈግ “ባጎረስኩ እጄን ተነከስኩ” የሚያስብል አሳፋሪ ተግባር ነውና! የአክሱም ሙስሊሞች ከግዞት ነፃ ሆነው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በአፋጣኝ መስጂድ የመሥራት ህግ-መንግስታዊ መብታቸውን እንዲያገኙ።

እንደ አክሱም ሙስሊሞች ሁሉ እዚያው ትግራይ ውስጥ የዱራ ልጆች አሁን ላለው ህግ-መንግሥት የህይወት መስዋዕትነት ከፍለው የተሰራውን የዱራ መስጂድ ማፍረሱ አይን-አይየው ጆሮ አይስማው የሚያስብል ዘግናኝና አሳፋሪ ተግባር በመሆኑ የፈረሰው የዱራ ነስጂድ ባስቸካይ ይገነባ።

አክራራኢና ፀጉረ-ልውጥ ሰባኪዎች ከኢትዮጵያውያን አንደበት ወጣ ለማለት በማያስደፍር ፀያፍ ስድብ የተከበረውን ቁርዓንና ኢስላም ተወዳጁን ነብያችን ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) ብሎም በዓለም ላይ ያሉ ሙስሊሞችን በሙሉ በመሃል አዲስ አበባ በሚገኙው ጊዮርጊስ በት-ክርስቲያንና በሌሎችም ቦታዎች ሲሰደቡ ሐይማኖትን ሲያራክሱ ፀብን ሲያጭሩ የሚያረጋግጥ የትባ መረጃ ቢኖርም “ጌታዋን የተማመነች በግ ላቷን ውጭ ታሳድራለች” ይባል ዘንድ ህግ የሚባለው የበላይ መመሪያ እስከ አሁን ስላላገኛቸው። ነብዩን፣ ቁርዓንን፣ ኢስላምን፣ ሙስሊሞችን ፀብ ለማጫር ያራከሱና የሰደቡ በአስቸኳይ ለፍርድ እንዲቀርቡ።

ያለን እንደሌለን አድርጎ ማየት፣ የተቆጠርን እንዳልተቆጠረ አድርጎ ቁጥርን ማዛባት ከተራ ማጭበርበር ተለይቶ አይታይም። የኢትዮጲያ ሙስሊም ህዝብ ከግማሽ በላይ ሆኖ ሳለ አዲስ በተደረገው የህዝብ ቆጠራ ሃያ ሚሊዮን የሚያደርሰው ሙስሊም ህዝብ ተቀንሶ የት ገባ? አዲሱ የህዝብ ቆጠራ የሙስሊሞችን የዜግነት መብት ለመሸራረፍ ሆን ተብሎ የተዘጋጀው የውሸት ቁጥር

First Hijra Foundation

በመሆኑ ብሎም ቁጥሩ የውስጥ ሴርነቱን የማንጠራጠር በመሆናችን፤ አዲሱን የህዝብ ቆጠራ አንቀበለውም፤ መንግሥትም ባስቸኳይ እንዲያስተካክለው በጥብቅ እናሳስባለን።

ውድ ወገኖቻችን ሆይ! ዛሬ ከስራና ከቤት አምጥቶ እዚህ ያሰባሰበን ለዘመናት በግልፅም በስውርም፣ በጩኸትም በሎሆሳስም የሚሰማው የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች የመብት ጥያቄ ነው። ጥያቄውም ለምንወዳት አገራችን ህልውና ወሳኝ ነው። የዚህ የመብት ጥያቄ ችላ መባል የአገራችንን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥሉ አደገኛ ችግሮች በአገራችን ላይ እንዲከሰቱ እያደረገ ነው።

በአዋሳ ዩንቨርሲቲ ቁራዓን ተቀዶ ለመሰዳጃ ሲውል ሙስሊም ተማሪዎች የሰለጠነና የታጋሽነት ባህሪያቸውን አሳይተው ወንጀል ፈፃሚውን ለህግ አካላት አሳልፈው ቢሰቱም ተድበስብሶ አለፈ። እንደ ዴንማርኩ ካርቶኒስት የነብዩ ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) ካርቱን የለበሰ በከምሴ በግልጽ ሲንቀሳቀስ ችግር ከመፈጠሩ በፊት መንግሥት የወሰደ እርምጃ አልነበረም። እንግዲህ ልብ ያለ ልብ ይበል! ቁራዓንን ቀዶ በማራከስ ለሰገራ መፀዳጃ መጠቀሙ የነብዩን (ሶ.ዐ.ወ.) የካርቱን ምስል ያለበት ቲ-ሸርት መልበሱ በሌላ አገር ተከስቶ ቢሆን ኖሮ የሚመዘዘውን መዘዝ መገመት ባያዳግትም የኢትዮጵያ ሙስሊሞች እልህ አስጨራሽ የሆኑ ፈተናዎችን አልፈዋል። ዛሬ ግን እዚህ የተሰበሰብነው ይህንን የመሰለው ፈተና ይብቃ ለማለት ነው።

የመቀሌ ዩንቨርሲቲ ክርስቲያን ተማሪዎች ስራዓተ-ሐይማኖትን የሚፈፅሙበት ቤተ-ክርስቲያን እያላቸው፤ ሙስሊም የመቀሌ ዩንቨርሲቲ ተማሪዎች ግዴታ የሆነውን ሶላት በመስገዳቸው ውይም ቁራዓንን ገልጠው በማንበባቸው ከትምህርት ቤት ተባረሩ። በጎጃም ውስጥ የቻግኒ ሙስሊም ተማሪዎች መስጂድ ሔደው ሲመለሱ ባላወቁት የነገር ወጥመድ እንዲገቡ ተደርገው ተግበስብሰው ለእስር በቁ። ሙስሊም ሴት ተማሪዎች ሐይማኖታቸው የሚያዘውን ሒጃብ መልበሳቸው (ፀጉራቸውን መሸፈናቸው) ጨዋ ሊያሰብላቸው የሚገባ ሆኖ ሳለ ሒጃብ እንዳይለብሱ የማይፈጠርባቸው ምክንያት የለም። ይህ የትምህርት ሚ/ር በሙስሊም ተማሪዎች ላይ ያነጣጠረው ኢላማና ከትምህርት ገበታቸው እንዲደናቀፉ ያደረገው መሰናክል ስለሚመስልበት የአያት-አባቶቻችን ሙስሊም በመሆናቸው ከትምህርት ገበታ የተደናቀፉበት ይበቃል። የትምህርት ሚ/ር ኢላማውን ለግንባታና ለብልፅግና፤ መሰናክሉን ለጎጂ፤ ለመጤና ለኋላቀር ባህሎች እንዲያደርግ እያሳሰብን በትምህርት ዓለም ውስጥ የአያት-የአባቶቻችን እጣ በኛ ዘመን አይደገምም እንላለን።

ህገ-መንግሥታዊ መብትን ተጠቅሞ በገዛ አገር ላይ መስጂድ መገንባቱ ለኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች እልህ አስጨራሽ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ወገኖች ተጠንስሶ ሆን ተብሎ የሚቀሰቀስ መዘዝም ይኖርበታል። ይህ ደግሞ የእምነት ነፃነትን ከመንፈግ ተለይቶ አይታይም። ስለዚህ ሙስሊሞች መስጂድ እንዳይገነቡ የሚደረገው አሻጥር ባስቸኳይ ይቁም።

አክራሪነት በማንኛውም የሐይማኖት ተቋም፣ የፖለቲካ ድርጅት፣ ወይም በአመለካከት ደረጃ ጣልቃ ሲገባ ወይም ሲገኝ- አክራሪነትን በጥብቅ እንቃወማለን። መንግሥትም ሆነ የሐይማኖት ተቋማት ሐይማኖቱን የሚተገብረውን አክራሪ በሚለው ፍርጃ ከመፈረጃቸው በፊት ክፉውን ከደጉ፣ ጥሬውና ብስሉን-ከደረቀው ሊለይ ይገባል። የኢትዮጵያን ሰላም ለማናጋት ሁከትን ለመፍጠር የተነሱ የክርስቲያን አክራሪዎች ኢትዮጵያ የከስቲያን ደሴት ናት፤ ዜግነት በመጠመቅ ብለው ቀረርቶ ሲያሰሙ፤ ይህንኑ ቅዠታቸውን የሚያንጸባርቅ ቲ-ሸርት ሲለብሱ፤ በራሪ ጽሑፎችን ሲበትኑ በገሃድ ተስተውለዋል።

First Hijra Foundation

የጎንደር ሙስሊሞች ውጡ ከአገራችን ሲባሉ ንብረታቸው ላይ አደጋ ሲጣል፤ መስጂድ ላይ ሲወረወር የመንግስት ዘገምተኛ እርምጃና የሐይማኖት ተቋማት ዝምታ የሚፈጥረውን ኪሳራ አስከፊ በመሆኑ የተፈራው ከመምጣቱ በፊት መንግሥት አፋጣኝ እርምጃ እንዲወስድ በጥብቅ እናሳስባለን።

በተመሳሳይ መልኩ በሐረር- በድሬደዋ፣ በሌሎችም የኢትዮጵያ ግዛቶች የአገርን ልማት የሚቀንሱ፣ የአገርን ሰላም የሚነሱ፣ ሁካታን የሚቀሰቅሱ ችግሮች እየተስተዋሉ ነው። አረም ካለ ምርት እንደሚቀንሰው ሁሉ በነግሥታዊ አሰራርና በሐይማኖት ተቋማት ውስጥ የበቀሉት አረሞች ይነቀሉ በማለት እነሆ ሰላማዊ ድምፃችንን እናሰማለን።

በመጨረሻም በሐይማኖት ተቋማት ውስጥ የመንግስት ጥልቃ ገብነት የሚኖረውን ጣጣ አርቆ በማሰብ የኢትዮጵያ መንግሥት ሙስሊሙ በነፃ መሪዎቹን የመምረጥ ዲሞክራሳዊ መብቱን እንዲጠበቅ ከማሰባሰባችንም ባሻገር መንግሥት በግልፅም በስውርም በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ጉባኤ (መጅሊሰል አዕላ) ዙሪያ የሚያጋራውን ጣልቃ ገብነት እንዲያቆም እንጠይቃለን።

እነሆ ዛሬ ለሰላም እዚህ ተሰባሰበን ከግማሽ በላይ የሚሆነውን የኢትዮጵያ ህዝብ በመወከል ለዘመናት ሲጠየቅ የነበረውን ጥያቄ በዲሞክራሳዊ መንገድ ጠይቀናል። ጥያቄአችን ወርቁም ሰሙም ዲሞክራሲ ነው። እውነትን ለመናገር ዲሞክራሲን እንረዳለን....ዲሞክራሲም ይገባናል። ግና ዲሞክራሲም ቢገባቸው እንዳልገባቸው ለሚያስመስሉ ወይም ዲሞክራሲን ለሚጠሉ ካበቃለት የፌውዳልና የኋላ ቀር ስርዓት፣ የዞረ-ድምር ዛሬም ያልወጡ፣ ያንንም ስርዓት በዛሬው ህይወት የሚቀይጡ እነርሱ ዲሞክራሲ እስኪገባቸው ወይም ካሉበት የነበረ ዓለም በዲሞክራሲ እስከሚነቁ ወይም ገና ለገና ይነቃሉ ብለን በነርሱው አለመረዳት እኛ እየተኮነን "ቻሉ ዲሞክራሲ እስኪገባቸው ነው እናንተ እኮ ቻይ ናችሁ" እየተባልን እየተደለልን የምንኖረው ህይወት በቃ በዲሞክራሲ ይለወጥ እንላለን።

የምንኖርበት ዓለም የዲሞክራሲ ስርዓት እደግ ተመንደግ ብላ ከመረቀችው እኛም እጆቻችን ዘርግተን አሚን እንላለን። እኛ ዲሞክራሲን የምንወድ በመሆናችን በዓለማችን ላይ ሻምፒዮን የሆንነን የዲሞክራሲ ፈለግ ተከትለን በደስታ እንጓዛለን። ይህም ማለት ጥያቄአችን በቂ መልስ ካላገኘን የዲሞክራሲን ፈር ተከትለን ለጥያቄአችን መልስ እንደምናገኝ ቁርጠኝነታችንን ለማረጋገጥ እንወዳለን።

ሰላም ለኢትዮጵያ!
እድገት ብልጽግና ለኢትዮጵያ!
ፍትህ ለተበዳዮች!
ነፃነት ለተጨቋኞች!

ኢንሻ አሏህ እንዲሆን እንታገላለን።

አመሰግናለሁ።

(ከፈርስት ሂጅራ የሰላማዊ ሰልፍ አስተባባሪ ኮሚቴ)

First Hijra Foundation